# የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው

በወታደራዊው ደርግ ዘመነ መንሥት ሕዝብ ለአምባ ገነኑ ባለው ከፍተኛ ጥላቻ የተነሳ በተሳሳተ መርሆ ላይ በመመርኮዝ ደርግን የተቀናቀነውን ሁሉ በማጀብ አላማውና ግቡን ሳይመረምሩ በደፈናው ደርግን ስላጠቁለት ብቻ ኋላ ሊያመጣ የሚችለውን ጣጣ ባለመገንዘብ የወያኔ የተገንጣይ ቡድንና እንዲሁም የሻቢያ የግንጠላ አምባሳደሮች በሕዝብ ጦር ላይ በሚያደርሱት ጥቃትና ጉዳት አለመቆጨት ከጦሩ ጋር አብሮ አለመቆም አልፎ ተርፎም ጦሩ እራሱ በአገዛዙ ላይ ካለው ጥላቻ በመነሳት ሚስጥር ለነኚህ የተገንጣይ ቡድኖች በማስተላለፍ ፣ ሳይዋጉ እጅ በመስጠትና የመሳሰሉትን ተግባራት ካለማወቅ በመፈጸማቸው ኤርትራም እንድትገነጠል ወያኔም ለጊዜው ባይገነጠልም ጊዜው አመቺ ሁኔታን ስለፈጠረለት መላ ኢትዮጵያን ቢቆጣጠር ተቀናቃኝ እንደሌለበት በመገንዘቡ በመላው ኢትዮጵያ ሀብት ለወደፊት ሊገነጥላት ያቀዳትን አንዲት አናሳ ክፍለ ሐገር በዘረፋ እንዲገነባ የተመቻቸ ሁኔታ በማግኘቱ የተቀረውን ኢትዮጵያዊ ሐብት በመዝረፍ ፣ በመግደል ፣ በማሰርና በማሰቃየት አሌ ለማይባል በደልና ስቃይ እየዳረገው ይገኛል ። ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ታዲያ መላው ኢትዮጵያዊና የቀድሞው የወታደራዊው መንግሥት ሰራዊት የተሳሳተ አመለካከትና ግንዛቤ እንደነበር ልናውቀው ይገባል። ይህም ሲባል የወታደራዊው መንግሥት ከተጠያቂነት ያመልጣል ማለት ሳይሆን ፣ መንግሥትን ምንም ያክል ብንጠላው ለወደፊት አገርና ወገንን ሊጎዳና ችግር ሊፈጥር ከሚችል ወገን ጋር መንግሥቱን ጠልተናል በሚል ሰበብ አብሮ መሰለፍና ማጫፈር ግን ኋላ ሊወጡት ወደማይችሉት ውድቀት ሊከት እንደሚችል ካለፈ ስህተታችን ተምረን አገርና ወገንን በማይጎዳ አሰላለፍ ተሰልፎ መንግሥትንም ሆነ ሌላን ኃይል በአንድነት መታገል የሚቻል መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

ዛሬ ይህንን ጽሁፍ ለመፃፍ ያነሳሳኝ ዋናው ጉዳይ ለረጅም ጊዜ በተቃዋሚ በኩል የተሰለፉ የፖለቲካ ኃይሎችም ሆኑ ሚዲያዎች እንደ ኦነግና ፣ ኦብነግ ያሉ በመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ አይደለንም ብለው የሚያምኑና አገር ለመገንጠልና ለማፍረስ የተነሱ ቡድኖችን በመደገፍ ፤ አብሮም በመሰለፍ የነሱን ተግባር በማግነን ለቅሷቸውን በማግነን ያዋቂ አጥፊ በመሆን ካለፈው የኤርትራ መገንጠል ትምህርት ባለመውሰድ ዛሬም ተመሳሳይ ስህተት ሲደገም በማየት ከልብ ማዘኔን ለማሳወቅ ነው ።

አገራችን አለመታደል ሆኖ በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ስር ወድቃ ከዚህ ቀደም ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ ሰቆቃ ውስጥ እንደምትገኝ ከማንም የተሰወረ አይደለም ፣ ይሄንን ለኢትዮጵያዊው ወገኔ መናገር ማለት ለቀባሪው አረዱት ይሆንብኛል ። ሆኖም ግን ወያኔ የሐገርና የሕዝብ ጠላት መሆኑን አስምሬበት ፣ መወገዱም የግድ መሆኑን ሳልዘነጋ ነገር ግን ገና ለገና ወያኔን አልወድም መወገድም አለበት የሚለውን በመያዝ ብቻ ለወደፊት አገርና ሕዝብን ይበልጥ ሊጎዳ ከሚችል ኃይል ጋር አብሮ መሰለፍ ካለፈው ስህተት አለመማርና አለማስተዋል ነው እላለሁ።

አንዳንድ በተቃዋሚው ጎራ ተሰልፈናል የሚሉ እንደ (ethiomedia) እንደ (EMF) እና የመሳሰሉ ድረገፆች ሰሞኑን የኦብነግ ሰራዊት ሰባት ከተሞችን ተቆጣጠረ ብለው በደስታ ሲያራግቡ ሳይ እውን እነኚህ የሚዲያ ባለቤቶች ከሕዝብ የተሰወረ የራሳቸው አላማ ይኖራቸው ይሆን? ብዬ እንድጠይቅ ተገድጃለሁ ። በመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ አይደለንም የሚሉ ፣ ኢትዮጵያዊነትን የሚኮንኑ ፣ መገንጠል ዋነኛና ቀዳሚ አላማቸው የሆኑን ቡድኖች መደገፍ ማለት ፣ ለምሳሌ የግብጽ ጦር የአባይን ውሃ በተመለከተ ኢትዮጵያን ቢወርና ከወያኔ ጋር ፍልሚያ ቢገባ ወያኔን ስለምንጠላውና እንዲወገድልን ስለምንፈልግ ብቻ ከግብጽ ጦር ጋር ማበርና አብረን መሰለፍ አለብን ማለት ይሆን? ይሄንን መልስ ለአንባቢያን እተወዋለሁ ። አሁንም ባረጀና ባፈጀ ፈሊጥ በመመርኮዝ "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" የሚለውን ከርካሳ ፍልስፍና ወደኋላ ትተን መታገል ያለብን ወያኔን ብቻ ሳይሆን መገንጠልን ከሚያቀነቅኑ ጠባብ ብሄርተኞችም ጭምር መሆኑን አስገነዝባለሁ ። "ተቀምጠው የሰቀሉት ቆሞ ለማውረድ ያዳግታል" የሚለው የአበው ተረት በኛ ላይ እንዳይተገበር እፈራለሁ ፣ የምንሰራውንና የምንቃወመውን በቅጡ እንመርምር ።

ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿ ትግል ነፃ ትሆናለች!

ከአይምሮ ዳኛቸው